0000- ሞባይል የሚሠራው በባንድ ሲሆን ባንዶችም በሦስት ከፍለን እናያቸዋለን

1. ባለ አንድ ባንድ - 900 MHZ
2. ባለ ሁለት ባንድ - 900/ 1800 MHZ
3. ባለ ሦስት ባንድ - 900/ 1800/ 1900 MHZ

ከነዚህ ውስጥ በሀገራችን አብዛኛው የምንጠቀምበት በባለሁለት ባንድ ነው።

ለምሣሌ፡- የሞቶሮላ፣የሣምሰንግ፣እንዲሁም የአንዳንድ ቻይና ሞባይሎች በባንድ ምርጫ ጊዜ ከተሳሳትን ኔትወርክ አይሠራልንም በዚህን ጊዜ ሲስተም ውስጥ ገብቶ ማስተካከል ያስፈልጋል።

Setting ⟶ Network ⟶ - 900/ 1800 MHZ

- 900 / 1900MHZ
- 900/ 1900 MHZ
- Automatic

እንደምርጫ ይሠጣሉ ስለዚህ መምረጥ ያለብን 900/ 1800 MHZ የሚለውን ነው። በቻይና ሞባይል ላይ እንደዚህ አይነት ምርጫ ከአለ 900/ 1800 MHZ ወይም አውቶ (Auto) የሚለውን መምረጥ ይቻላል።

- ሴሪያል ናምበር (IMEI) ኢንተርናሽናል ሞባይል ኢኩይፕመንት አይደንቲቲ ማለት የቀፎአችን መለያ ቁጥር ማለት ነው። የሚገኘው ባትሪው ከወጣ በኃላ IMEI - 354…… 15 ዲጂት ሆኖ እናገኘዋለን አሊያም *#06# ቁጥሮችን ስናስገባ ስክሪኑ ላይ ይፅፍልናል እነዚህ ቁጥሮች ለቀፎው የራሱ ኔትወርክ መለያ ቁጥሮች ናቸው።
- ሞባይሎች መለያ ቁጥር መነሻ 0፣1፣2፣3፣4፣5፣6 ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በ 35 የሚጀምሩ ጥሩ ሞባይሎች ሲሆኑ እኛ አገር አልስራም ሲሉ በፍሪካልኩሌተር አሊያም በሶፍት ዌር ይስተካከላሉ በ01 የሚጀምሩ ሞባይሎች በሃገራችን ውስጥ ምንአልባት በሶፍትዌር ሊሰሩ ይጭላሉ።
-

<u>ሞባይሎች የተሰሩበት ኮምፖነንት</u>

ኮምፖነንቶች በሁለት ይከፈላሉ

1- አክቲቭ

2- ፓሲቭ

- አክቲቭ የሚባሉት ንጌቲቭና ፖዚቲቭ ያላቸው ሁነው የተሰጣቸውን ቮልቴጅ መቀያየር የሚችሉናው። ለምሳሌ ትራንዚስተር፤ዳዮድ፤እይሲ
- ፓሲቭ የምንላቸው የተሰጣቸውን ቮልቴጅ መጨመር የማይችሉ ናቸው።ለምሳሌ ረዚስተር፤ኢንዳክተር፤ካፓሲተር

ሬዚስተር

አገልግሎቱ የኤሌክትሪክ ፍሰትን የሚቃወም ሲሆን።

ምልክቱ —R—▶

ኤሌክትሪካል ምልክቱ ——▶

መለኪያው ——▶ አህም (Ω)

ሲለካ

1- መጀመሪያ መልቲ ሜትሩን መምረጥ 3- ዜሮ እና ድምፅ ካነበበ ተበተበላሸታል

2- ከኤሌክትሪክ ጋር ያለውን ግንኙነት ማቃረጥ 4- ሬዚስተሩ አንድ ካነበበ ተበላሸታል

5- ሬዚስተሩ ትክክለኛውን ቁጥር ካነበበ ይሠራል።

የፊውዝ አለካክ

1- ፊውዝ ዜሮን(ድምፅ ከአነበበ ይሠራል 2- ፊውዝ አንድን ከአነበበ አይሠራም

የፊውዝ ምልክት በሞባይል ላይ

የተበላሸ ፊውዝ ለመስራት በሊድ እንቀባዋለን።

ካፓሲተር

- ካፓሲተር የኤሌክትሪክ ኃይልን ሰብስባ የሚያስቀምጥልን ነው።እንዲሁም በተለለያዩ ቦታወች እየተቀመጠ የማጣራጥ ሥራኝ ይሰራል።

ኤሌክትሪካል ምልክቱ

ሲለካ

1- መልቲ ሜትር መምረጥ
2- ከኤሌክትሪክ ጋር ያለውን ግንኙነት ማቃረጥ
3- አንድ እግሩን መንቀል
4- ካፓሲተር ከመለካቱ በፊት ቻርጅ ያደረገው መመጠጥ አለበት
5- ካፓሲተሩ ዜሮን ካነበበ ተበላሽቶዋል
6- ካፓሲተሩ አንድን ካነበበ ተበላሽቶዋል
7- የሚያነበው ቁጥረ እየጨመረ ከሄደ ይሠራል

ኢንዳክተር

ኢንዳክተር አገልግሎ የኤሌክትሪክ ፍሰትን ማስተላለፍ ነው እንዲሁም የማጣራት ስራን ይሰራልናል።

ኤሌክትሪካል ምልክቱ

ሲለካ

1- መልቲ ሜትር መምረጥ
2- ከኤሌክትሪክ ያውን ግንኙነት ማቃረጥ
3- አንድ እግሩን መንቀል
4- ኢንዳክተር ድምፅን ከሰጠች ይሰራል
5- ኢንዳክተሩ አንድን ከአነበበ አይሠራም

ዳዮድ

ዳዮድ የተለያዩ ስራወችን ስራዋችን የሚሰራ አክቲቭ ኮምፖነንት ነው።ለምሳሌ ኤሲን ወደ ዲሲ ይቀይራል፤ኤሌክትሪካል ኢነርጂን ወደ ላይት ኢነርጂ ይቀይራል፤ከ220 ኤሲ ቮልቴጅ ወደ 110ኤሲ ቮልቴጅ ቀይራል።

ዳዮድ በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚሠራ ነው።ፖዚቲቭ ለፖዚቲቭ እና ነጌቲቭ ለነጌቲቭ ሲሰጠው ሀይል ያስተላልፋል ።ከሁለት ነገሮች ቅልቅል የተሰራ ነው። እነርሱም ከሲልከን እና ከጀርመኒየም የተሠራ ነው።

ኤሌክትሪካል ምልክቱ

ሲለካ

1- መልቲ ሜትር መምረጥ
2- ከኤሌክቲሪክ ጋር ያለውን ግንኙነት ማቃረጥ
3- አንድ እግሩን መንቀል
4- ዳዮድ ዜሮን ከአነበበ አይሠራም

ትራንዚስተር

5- ዳዮድ አንድን ከአነበበ አይሰራም

6- ዳዮድ በአንድ በኩል ቁጥር በሌላ በኩል አንድን ከአነበበ ይሰራል።

አነስተኛን የኤሌክትሪክ ፍሰት ወደ ከፍተኛ የሚለውጥልን ነው። ለምሳሌ ፍሰቱን ፣ሀይሉን ፣አቅሙን ቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚያሳድግልን ትራንዚስተር ነው።

ትራንዚስተር ሶስት እግር እና ሁለት መገጣጠሚያዎች አሉት እግሮቹ ኢሚተርሏE / ቤዝሏB/ እና ኮሌክተርሏ C/ ናቸው። በስዕል ሲገለፅ

ሲለላ

1- መልቲ ሜትር መምረጥ

2- ከኤሌክትሪክ ጋር ያለውን ግንኙነት ማቃረጥ

3- አንድሏሁለት እግሩን መንቀል

4- ትራንዚስተሩ ዜሮ ከአነበበ አይሠራም

5- ትራንዚስተሩ አንድን ከአነበበ አይሠራም


6- ትራንዚስተሩ የኢሜትር ቤዝ የሚያነበው ከኮሌክተር ቤዝ ከሚያነበው ሲበልጥ የሚሠራ ነው።

አይ ሲ

አይ ሲ ማለት ከላይ ከተጠቀሱት ከኮንዳክተር በስተቀር ሌሎቸን በውስጡ አቅፎ የሚይዝ ነው። አይ ሲ ከተበላሸ ማለትም እርስ በእርሱ ከተያያዘ በእጃችን ስንነካው የሙቀት ስሜት ያሰማናል።

- ለሞባይል ጥገና የምንጠቀምባቸው መሣሪያዎች

ሞባይል መስራትና አለመስራቱን የምንሞክርበት መሣሪያ ፓወር ሰፕላይ እንለዋለን።



1- ፓዘቲቭ ገመድ የሚገባበት

2- ነጋቲቭ

3- ኔትወርክ የምንለካበት


4- ለሞባይሉ የሚሠጠው ሀይል በዲጂታል / በቁጥርሏ

5- ለሞባይሉ የሚሠጠው ሃይል በአናሎግሏበምስልሏ

6- የሚንቀሳቀስ የሃይል ፍሠት

ይህ መሣሪያ የሚረዳን ፀጥ ብሎ ለመጣ ሞባይል ምልክት በመስጠት ለመፍትሔ ይረዳናል። ይሄም መሣሪያ ሁለት ዓይነት ሲሆን አንደኛው መፍትሄውን በአናሎግ ሲያስረዳን ሌላኛው በቁጥር / በዲጂታልሏያስረዳናል።

A- **<u>የአናሎግ ፓወር ሳፕላይ</u>**



ከላይ በተገለፀው መልኩ ከፓወር ሳፕላይ 3.6 V ሰጠን ሞባይሉንና ፓወር ሳፕላየን አገናኝተን

1- የሞባይሉን ማብሪያ ማጥፊያ ስንጫነው የፓወር ሰፕላዩ ከረንት ኢንዲኬተር ወደፊት ሄዶ ወደ ኃላ ከተመለሰ ሞባይሉ ምንም ችግር የለበትም

በፍትሄ / solution/

- ባትሪ መቀየር
- አጥቦ ማሞቅ
- ምንአልባት የሶፍቴ ዌር ችግር

1. የሞባይሉን ማብሪያ ማጥፊያ ስንጫነው የፓወር ሰፕላዩ ከረንት ኢንዲኬተር ወደፊት ሄዶ ከዚያው ከቀረ ሞባይሉ ላይ ያሉ ኮምፐነንቶች ሾርት የሆነ አለ ወይም የኮምፓነንቶች እግርና እግር በቆሻሻ የተገናኘ አለ

መፍትሄው / solution/

- ካፓሲተርን እና ዳዮድን ቼክ ማድረግ
- አጥቦ ማሞቅ

2. የሞባይሉን ማብሪያ ማጥፊያ ስንጫነው የፓወር ሰፕላይ ከረንት እንዲኬተር ካልተንቀሳቀሰ ሞባይሉ የማብሪያ ማጥፊያ / switch ችግር አለበት

መፍትሄ / solution

- ስዊችን መፈተሽ
- ስዊች መንገድን መፈተሽ
- ፓወር አይሲን መስራቱን ማረጋገጥ

3. የሞባይን ስዊች ሳንጫነው የፓወር ሳፕላይ ከረንት ኢንዲኬተር ሄዶ ከተመለሰ ሞባይሉ የሶፍት ዌር ችግር አለበት

መፍትሄው / solution- በሶፍት ዌር ፈለሽ ማድረግ

4. የሞባይሉን ስዊች ሳንጫነው የፓወር ሰፕላይ ከረንት ኢንደኬተር እየጮኸ ሄዶ ከተመለሰ እዚያው ሄዶ ከቀረ ሞባይሉ የመስራት ተስፋው የመነመነ ነው

መፍትሄው / solution

ምን አልባት አጥቦ በማሞቅ መሞከር አለበለዚያ ግን CPU or PIC is sorted

B- የዲጂታሉ ፓወር ሳፕላይ

ከረንቱ - 0.00 ከአነበበ የተለያየሏየተቆረጠ መስመር አለ

“ - 0.01- 0.06 ከአነበበ የሶፍት ዌር ችግር አለ

“ - 0.06 - 0.35 ከአነበበ የሚሠራ ሞባይል ነው

“ - ከ0.45 በላይ ከአነበበ ቦርዱ ሾርት አለው።

ሞባይልን ስንሰራ የምናሞቅበት፣የምንቀቅልበት፣የምንበይድበት ሆት ኤር ጋን ይባላል።

1- መበየጃ

2- የመበየጃ ሃይል መጨመሪያ

3- የመበጀያ ማብሪያ ማጥፊያ

4- የማሞቂያ ማብሪያ ማጥፊያ


5- የማሞቂያ ንፋስ መጨመሪያ

6- የማሞቂያ ሃይል መጨመሪያ

7- ማሞቂያ

8- የመበየጂያ ሃይል ማንበቢያ

9- የማሞቂያ ሃይል ማንበቢያ



የአይሲ አይነቶች

ፓወር አምፕሊፋየር / power Amplifier /

- በሞባይል በምንደውልበት ጊዜ ወዲያውኑ ሞባይሉ የሚጠፋ ከሆነ ፓወር አምፕሊፋየር ነው።

ከላይ ለተጠቀሱት መፍትሄ

- ሞባይሉን በኬሚካል / Dulentine/ በተባሉ ከታጠበ በኃላ በሆት ኤር ጋን ጥሩ ንፋስ በመስጠት በአነስተኛ ሙቀት በመስጠት ማስተካከል ይቻላል።

የፓወር አይሲ / Power IC/ መለያ

- ዙሪያውነ በኮምፐነንት የታጀበ ነው። በብዛትም ካፓሲተሮች ይታያሉ እንዲሁም በአጠገቡ ሪል ታይም ክሎክ / RTC / የምትባል በወርቃማ፣በጥቁር፣በነጭ ቀለም የተቀባች ትገኛለች።

- በአይሲው ላይ UEM, CCONT, RETU, PIC ተብሎ ከተጻፈበት እነዚህን ምልክቶች ብዙጊዜ የምናገኛቸው አይሲው ላይ እንዲሁም በመፀሃፍ ላይ በአሉ ዲያግራሞች ነው። RETU ሚለውን ብዙ ጊዜ የምናገኘው በኮምፒዩተር ላይ ዲያግራም ስናነብ መለያ አድርገውት ይገኛል።

በሞባይል ላይ ያሉ የሚሞሪ IC በሁለት ይከፈላሉ

A - **ሮም አይሲ / ROMIC/ Read only memory integrated circuit** / ይህ አይሲ ቃሚ የሆኑ ፕሮግራሞችን የሚጫኑበት ሲሆን እነዚህም ሲስተሞች ለምሳሌ setting, message, contact…..

B- ራም አይሲ / RAMIC/ Randum Access memory ጊዜአዊ የዳታ ፕሮግራሞችን የሚይዝልን Temporary storage data/ ሲሆን በሁለት ይከፈላል።

ስታቲክ ራም / static RAM/

- ሚስኮል / Missed call
- የተቀበልነውን / Received call
- የደወልነውን / Dialed call

ሰብሰቦ የሚያሳየን ሲሆን ስታቲክ ራም ከተበላሸ ከላይ የጠቀስናቸውን ማግኘት አንችልም ማለትም

1. ሚስኮልሏ Missed call
2. የተቀበልነው ስልክ / Received call
3. የደወልነው ስልክ አይገኝም / Dialed callሞባይሉ ቫይረስ ያለበት ከሆነ ከላይ የተገለፁትን ላያሳን ይችላል በመሁኑም ሞባይለን ፎርማት ማድረግ ይጠበቅብናና። ለምሳሌ ኖኪያ n71, 73 የመሳሰሉትን በለሂ 7370# ፎርማት ማድረግ ይቻላል


- **የሪል ታይም ክሎክ / RTC**

- ከፓወር አይሲ ከ 1.6v እስከ 1.8v ከተሰጣት በኃላ 32.768 KHZ ያመነጫል
- 32.768 KHZ ከአመነጨ - ሞባይሉ ኔትወርክ በትክክል ይሠራል
    - ሰዓት በትክክል ይሰራል
    - መጭ ጥሪ በትክክል ይሠራል።

*** ኦዲዩ አይሲ / Audio IC/ ይህ አይሲ ከተበላሸ**

- ድምፅን ማስተላለፍ አይቻልም
- ድምፅን መቀበል አይችልም
- ድምጽ በጥሩ ሁኔታ አይደርስምሲይቀንሳል

- **ቻርጀር አይሲ / charger IC/** ከተበላሸ ስልካችን ቻርጅ ማድረግ አይችልም ከብዙዋች ሞባይሎች ላይ ቻርጀር አይሲ ከፓወር አይሲ ውስጥ ይገኛል።
- **ዩአይ ሪንገር አይሲ / UI or Ringer IC/** ይህ አይሲ 20 እግር ያለው ሲሆን ከሁሉም ሞባይል አናገኘውም። አገልግሎቱም ፡-
    - **ሞባይሉ ጥሪ ሲመጣ**
        - ቫይብሬተር ማሰማት
        - ጥሪን ማሰማት
        - ለሞባይሉ ብርሃን / light/ መስጠት
    - ዩአይ ሪንገር አይሲ በአንድ በኩል 10 እግር በሌላ በኩል 10 እግር አለው።



ከ + ፓወርየመጣ

ቁጥር	አይሲ	መለያ	መገኛ ቦታ

1	ዲስፕሌይ አይሲ	ብርማ ክለር ያለው ሆኖ የሚያንጸባርቅ ሲነቀል ሙሉ / 25/ እግር ያለው።	ዲስፕሌይ አይሲ ያላቸው ስልኮች ላይ ሆኖ ሲናነው። 1.ስክሪኑ መለኪያ አጠገብ 2. በስክሪኑ መለኪያ አቅጣ 3. በሲፒዩ ውስጥ
2	ብሉ ቱዝ አይሲ	1. በሲልቨር የሚያንጸባርቅ ሆኖ አጠገቡ ነጭ ኮምፐነንት ትገኛለች 2. በጥቁር ሆኖ አሁንም አጠገቡ ነጭ ነገር ትገኛለች። ጥቁር ነጭ	ብሉቱዝ መቀበል የሚችሉ ስልኮች ላይ ብቻ። አንዳንድ ስልኮች ላይ ኤፍ ኤም አይ ሲ በቆርቆሮ ተሸፍነው ሊገኙ ይችላሉ።
3	ኤፍ ኤም አይሲ	1. በሲልቨር ሆኖ የሚያንፀባርቅ ሲሆን አጠገቡ ከለራቸው ለየት ያሉ ሁለት ወይም ሶስት ኢንዳክተሮች ይገኛሉ። 2. በጥቁር ሆኖ አጠገቡ አሁንም ሁለት ወይም ሶስት ከለራቸው የተለየ ኢንዳክተሮች ይገኛሉ። ጥቁር	
4	ካሜራ አይሲ	1. በጥቁር ይሆንና አጠገቡ ቡስተር ኮይል የሚገኙበት 2. አሁንም በጥቁር ሆነ በአይሲው ዙሪያ ብዛት ያላቸው ኢንዳክተሮች ይገኛሉ።	1. ካሜራው ያለበት አጠገብ 2. በካሜራው መከሊያ ቦታ 3. በሲፒ ውስጥ
5	ሚሞሪ ካርድ አይሲ	1. በሲልቨር የሚያንጸባርቅ እና በጥቁር አይሲ አብረው 2. አንድ አይሲ ብቻ ካገኘን	1. ሚሞሪ ካርድ የሚገባበት ቦታ አጠገብ 2. በሚሞሪ መሰኪያው አካባቢ

በሞባይል ላይ የሃረድ ዌር ብልሽቶች

1. የቫይብሬተር ብልሽት

ጥሪ ሲመጣልን የሚነዝረን ቫይብሬተር(Vibra) ይባላል።

ዩአይ / ሪንገር አይሲ በአላቸው ሞባይሎች ቫይብሬተር እንቢ ከአለ


1ኛ. ቫይብሬተሩን በኮንቲኒቲ መለካት ድምጽ መስጠት አለበት

2ኛ. ቫይብሬተር ከሚቀመጥበት / vibra pad/ ላይ ዝገት ወይም የተላጠ አለመሆኑን ማረጋገጥ

3ኛ. ለሞባይሉ በፓወር ሰፕላይ ከ 3.6v – 4v ሰጥቶ ከቫይብር መቀመጫው ላይ የተሰጠው ቮልቴጅ መድረሱን ማረጋገጥ

4ኛ. ዩአይ / ሪንገር አይሲ ከ 16ኛ እግር እሰከ ፊውዝ / fuse/ ከፊውዝ እስከ ቫይበር መቀመጫው ድረስ ያለውን መስመር በኮንቲኒቲ መለካት ከላይ የተጠቀሱት ሠርተው አሁንም አልመጣም ከአለ **ዩአይ** አይሲ ከሲፒዩ ጋር **ተለያይቶዋል።**

መፍትሄው ፤- አይስተካከልም



2. .የጥሪ ብልሽት (ሲጠራ አለመሰማት)/ ባዛርሊለዉድ ሰፒከር

2.1 በድሮ ሞባይል ላይ ባዛር ተበላሽታል

ሀ. ባዛሩን / Buzzer በሜትር ድምጽ መስጠቱን መለካት


ለ. የባዛር መቀመጫው ዝገት መኖሩን፣መላጡን ማረጋገጥ

ሐ. ለሞባይሉ ከፓወር ሰፕላይ ላይ ከ3.6v - 4v ሰጥቶ ከባዛር መቀመጫ ላይ የተሰጠውን ቮልቴጅ ማንበብ

መ. ከዩአይ / ሪንገር አይሲ **ከ6ኛው** እግር **እስከ ባዛር** መቀመጫው ድረስ መስመሩን መለካት

ሠ. Ring የሚያርፍበትን ቦታ ማጽዳት ከላይ የተመለከትነው ሶስት ነጥቦች **ለሁሉም አንድ** ናቸው

ዲሲቲ 3 / Dct 3/



ሪንገር የሚያርፍበት ቦታ

(inter face)

2.2 .ላወድ ስፒከርን መፈተሸ(የጥሪ ድምፅ አለመስማት)

በዘመናዊ ሞባይሎች ላይ

ሀ. የላውድ ስፒከር / laud speaker መገናኘቱን ቼክ ማድረግ

ለ. ላወድ ስፒከርን መፈተሸ

ሐ. ሲስተም ውስጥ ገብተን ጥሪውን **ኦፍ/off** አለማድረጋችንን ማረጋገጥ ለምሣሌ፡- setting → tone → incoming call → on/ off or silent, only vibra የሚሉትን መርጠን ከሆነ ማስተካከል።በድሮ ሞባይሎች ላይ message setting screensaver on/ off የሚለውን ቼክ ማድረግ

መ. ላውድ ስፒከርን በሜትር ለክተን ድምጽን እና ከ**7- 12Ω** ማንበቡን ማረጋገጥ። ካላነበበ በአዲስ መተካት / replace by newone

ሠ. ከላውድ ስፒከር መቀመጫ ላይ ለክተን ድምፅ አለመኖሩን ቸክ ማድረግ። ድምፅ ከሰጠ ማፅዳት የተበላሸ ካፓሲተር መፈተሸ እንዲሁም ሙዚቃ ከፍተን ከመቀመጫው ላይ በመልቲ ሜትር ስንለካ ድመጥ ከአለ መስመር አለመበላሸቱን ማረጋገጥ።

3. ተደውሎልን በምናወራበት ወቅት አለመስማት(ስፒከር)

ሀ. ስፒከርን በሜትር ድምጽ መስጠቱን ማረጋገጥ እንዲሁም ድምጽና ቁጥር ማንበብ አለበት ኦርጂናሎች የሚያነቡት ከ**27Ω- 34Ω** ሲሆን አንዳንዴ 7Ω እያነበቡ ይሠራሉ አለበለዚያ በአዲስ መቀየር።Replace by newone/

ለ. የስፒከርን መቀመጫ / speaker pad / ማጽዳት

ሐ. የስፒከር እግሮች በትክክል ከመቀመጫው ጋር መገናኘታቸውን ማረጋገጥ

መ.የስፒከርን መንገድ ተከትሎ ማስተካከል

ሠ. የተቃጠለ ካፓሲተር አለመኖሩን ማረጋገጥ

ማጠቃለያ፡- ላውድ ስፒከርም ይሁን ስፒከር በትክክል እያነበበ ጥሪ ሲመጣም ይሁን ስናወራ ብዥብዥ የሚል ድምጽ ከሠማን ከውስጥ ያለው ሽቦ ሲግናል ሲመታው ሰለሚበተን የሚረብሽ ድምጽ ይሰጣል፡

መፍትሄው መቀየር Replace

- ካፓሲተር ሾርት አለማድረጉን ማረጋገጥ

4.ስናወራ የእኛ ድምጽ አለመሰማት(የማይክ ብልሽት)


- ማይክ / Mic/ ቼክ ማድረግ የሚሠራ ማይክ ከሆነ በሜትር ስናነበው በአንድ በኩል **ከ500- 900Ω** ማንበብ

አለበት በሌላ በኩል አንድ(1) አሊያም አነስተኛ ቁጥር ያነባል። በሁለቱ በኩል አንድን ከአነበበ አይሠራም


- ማይክ የሚያርፍበትን / Mic pad/ ማጽዳት
- የማይ መንገዶችን መከተል
- የማይክ መቀመጫ ድምፅ አለመስጠቱን ማረጋገጥ

ሁለት ዓይነት የማይክ መንገዶች አሉ

A - በሁለት ኢንዳክተር የሚሄዱ



B በአንድ ኢንዳክተር የሚሄድ



- L- inductor የተረበሸ ድምጽ ከመጣ ታጣራለች / filtering noise voice/
- ካፓሲተር ሾርት / short ካደረገ የማይክ ነጋቲቭ እና ፓዘቲቭ ስለሚገናኝ ካፓሲተርን ቼክ ማድረግ
- መስመሮቹ ካልሠሩ በጃምፐር መዘርጋት

ከላይ የተጠቀሱት በሳምሰንግና በቻይና ሞባይል ላይ ከአሣዩ የስፒከር የላውድ ስፒከር ኬብሎችን ማስተካከል።

- **<u>ከስልካችን ስክሪን ላይ የሄድፎን (Ω) / Head ምልክት ከአለ / ከአሳየ</u>**

ሞባይሉን በሲስተም ማስተካከል

የኢርፎን እግሮች እርስ በርሳቸው በቆሻሻ ስለሚገናኙ ማጽዳት ወይም መቀየር አሊያም

ሞባይሉ ሴቲንግ ውስጥ ገብቶ ሪሰቶር ፋክቶሪ ማድረግ ማለትም እነደፋብሪካው ማድረግ

- **<u>ስልኩ የሚንጫጫ ድምፅ ከአለው</u>**

እኛ ስናወራ ከሆነ / during sent out

- ማይክ መቀየር / Replace of mic
- የማይክ መቀመጫንሏmic pad/ ማጽዳት
- ከማይክ መንገድ ያለውን ኢንዳክተር ቼክ ማድረግ ማለትም የማጣራት ስራውን ትቶ ከሆነ

ጥሪ ስንቀበል ከሆነ

- ስፒከር መቀየር
- የስፒከር መቀመጫውን ማጽዳት
- ኢንዳክተሮችንና ካፓሲተሮችን ቼክ ማድረግ

ከላይ ከተገለጹት ችግሮች በተጨማሪ ሲስተሙን በሜኑ ፍለሽ ወይም ሪስቶር ፋክተሪ መስራት ይቻላል፡

ለምሣሌ፡-

12345 ለኖኪያ

1234 ለሞቶሮላ

0000፣00000፣00000000፣1123 ለሳምሰንግ

0000፣00000፣00000000፣1122፣1234፣12345፣22444፣22244፣44222፣44422፣3344፣ 5678 ለቻይና እነዚህ ቁጥሮች ፋብሪካው የሠጣቸው ናቸው::

4.የኔት ወርክ ብልሽት

- የሞባይል ኔት ወርክ አልሠራም ከአለ የምንፈትናቸው

4.1.አንቴና

ከሞባይላችን በላይ በኩል ከከቨሩ ጋር ተያይዘው ባለሁለት ወይም ባለ 3 እግር ብረቶች ናቸው እነዚህ ብረቶች -

- የዝገት
- የመጣመም
- የመቆረጥ
- ብረቶች ከኔትወርክ መቀመጫው ጋር በትክክል ካለመገናኘት ችግር ከአለባቸው በስልካችን በምናወራበት ወቅት የመቆራረጥ ባህሪ አላቸው

መፍትሄ /

- ዝገት ያለበትን በዱለንቲን ማጽዳት
- የተጣመመን ማቃናት
- የተቆረጠን በመበየጃ መቀጠል አሊያም መቀየር
- ብረቶች ከሞባይሉ ቦርድ / ጋር በትክክል መገናኘታቸውን ማረጋገጥ

4.2 የአንቴና ስዊች(ኔትወርክ አይሲ)

የአንቴና ስዊች በከፊል ከተበላሸ ጥሪ ሲመጣ ወይም ደውለን በምናወራበት ወቅት የኔት ወርክ ባር ቀስ በቀስ እየቀነሰ ሄዶ መጨረሻ ላይ ኔትወርክ ባሩ ባዶ ሆኖ ግንኙነት ይቃረጣል።

መፍትሄው/

ቦርዱን አጥቦ አንቴና ስዊችን ማሞቅ አንቴና ስዊች የሚገኘው የአንቴና እግር ከሚያርፉበት ወረድ ብሎ እናገኘዋለን።

አንቴና ስዊች ሙሉ በሙሉ ከተቃጠለ ETC የሚል አይገኝም።

መፍትሄውሏ

- አጥቦ በማሞቅ መሞከር
- አንቴና ስዊችን መቀየር

4.3 አር ቲሲ

በሞባይል ላይ ያለች ከቦርዱ ከ1.6 እስ 1.8 **32.768** ታመነጫለች። በትክክል ካመነጨች

- ኔትወርክ
- መጭ ጥሪ
- ሰዓትን ይቆጣጠርልናል።

ስልክ በምናወራበት ጊዜ ኔትወርክ ባር አንድ ጊዜ ባዶ አንድ ጊዜ ፉል

መፍትሄሏ

- ሞባይሉን ማጠብና ማሞቅ
- RTCን ከተመሣሣይ ሞባይሎች አንስቶ መተካት

ሙሉ በሙሉ ከተቃጠለች

- ኔትወርክ ይጠፋል

- ሰዓታችን በትክክል አይሰራም
- መጭን ጥሪ በትክክል አያስተናግድም
- ምንአልባት ሞባይሉ ሊጠፋ ይችላል

4.4 ፊልተር filter

ፊልተር ሲቃጠል ስልክ በምናወራበት ጊዜ የሞባይል ኔት ወርክ ደረጃ በደረጃ እየቀነሰ ሄዶ እንደገና እየጨመረ ከመጣ የፊልተር ችግር ነው።

መፍትሄው / solution


- ማጠብና ማሞቅ / to clean and to give slightly heat
- መቀየር / Replace

5.የ ሲ ም ች ግ ር

ሀ.የሃርድዌር ችግር / Hard ware problem/

- የሲምን አባራ መጥረግ
- የሲም ማስቀመጫዎችን በትክክል ማጽዳት፣አለመሠበራቸውን ማረጋገጥ፣ አለመጣመሙን ማረጋገጥ ከሲም መቀመጫዎች ውስጥ አንዱ እግር ከግራውንድ ጋር መገናኘቱን ማረጋገጥ

አንዳንድ ሞባይሎች ላይ የሲም ማረፊያው እንደሚከተለው ይገኛል።



ሲሙን አስገባ ሲለን / insert sim ሲለን

1. የሞባይሉን ስክርው ማጥበቅ


2. በወረቀት ሲሙን መጫን
3. ሲሙን በትክክል አቅጣጫው ማስገባት
4. የሲም አይሲ(Sim IC በ Dct3 ሞዴሎች ላይ ከላይ ባንድ በኩል 2 ባንድ በኩል 3 እግር አላቸው።
5. በDCt4 ሞዴሎች ላይ የምትገኘው ከሲም ማረፊያው አካባቢ ነው። ሲታይ ያንጸባርቃል 8 እግር አላቸው።

መፍትሄ፡-

- ❖ አጥቦ በማሞቅ መሞከር
- ❖ ሲም አይሲን መቀየር

A Sim Card have six pads that also corresponds to the six SIM connectors pins, but only five has totally have connection on the entire layout.

SIM DATA - this is a digital data that being stored on a SIM memory
SIM Clock - this is a clock frequency signal that being synchronize to the digital data to create data signal in order transfer or sends and receive data information.
SIM Reset - this is also a frequency signal that triggers or reset all synchronization process.
VSIM B+ Supply Voltage- This a power supply voltage used to activated the SIM circuit.
SIM Ground - a ground line voltage
The other one is not connected



A Typical block Diagram above shows on how SIM Circuit Works on a Cellular

phones circuits.

የፓወር አይሲ ችግር / power IC problem/

ፓወር አይሲ ከተበላሸ “ በ *#06# “ሴሪያል ቁጥሩን ስናውጣ 000 ...ወይም??? ካመጣ ፓወር አይሲን መቀየር


ለ - ሶፍት ዌር ችግር

1. ካርዱ ችግር አለበት / card error/
2. የማይጠቅም ሲም ካርድ / invalid sim card/
3. የተሳሳተ ሲም ካርድ / wrong sim card/
4. ካርዱን አልቀበልምሲ sim card not accepted/
5. ትክክለኛወን ሲም ካርድ አስገባ / Insert correct sim card እና ሌሎችንም ከአለ በሶፍት ዌር ይስተካከላል። በሶፍትዌር ሲባል አንሎክ / unlock ይደረጋል።

- ሲም ካርድ የአንድ ሠው መለያ ቁጥር ማለት ነው
- ሲም ካርድ መቶ እና ከዚያ በላይ ስሞችንና ቁጥሮችን ሲመዘግብልን ከ 15 በላይ መልዕክትን ይይዛል።

የሲም ካርድ ችግር


1/ Insert SIM



“Insert sim” ከአለን የምንወስደው ማስተካከል


- ስሙን በትክክል ማስገባት
- የቀፎውን እስክሪን ማጥበቅ
- ወረቀት መጠቀም
- አጥቦ ማድረቅ


በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱት አልመጣም ከአለ የሲም IC ከተነቀለ በኃላ መስመሮችን መፈተሸ



እነዚህን ሞክረን እንቢ ከአለ በኮምፒውተር ማስተካከል


2/ Sim not accepted






“Sim not accepted” ሲለን ከላይ የተጠቀምናቸውን መፍትሄዎችን እንወስዳለን። ቢሆንም ግን መፍትሄ ካልሀነን በኮምፒውተር ማስተካከል ያስፈልጋል።

3/ Sim rejected




“Sim rejected” ከተባልን በሶፍት ዌርኧበኮፒውተር ይስተካከላል።

4/ Sim invalid



“Sim invalid” ከአለን መጀመሪያ በ “*#06# “ሴሪያል ቁጥሩን እናመጣለን። ሴሪያል ቁጥሩ ትክክለኛ ቁጥሩን ከፃፈልን በኮምፒውተር የሚስተካከል ሲሆን ሴሪያል ቁጥሩ በጥያቄ ምልክት(????....) ወይም በዜሮ ተጽፎ ከመጣ በኮምፒውተር ሶፍት ዌር መስተካከል አለበት።


5/ ለቦርድ ሞባይል



Not smart SIM

“not smart Sim”ከተባለ መኮምፒውተር ሶፍት ዌር ይስተካከላል።

6/ ለሞቶሮላ ሞባይል



Check card

“check card” ብሎ የሞቶሮላ ሞባይል ከመጣ በኮምፒውተር ሶፍት ዌር ይስተካከላል።

ሞ ባ ይ ሎ ች

ቴስትሏTest mode / ወይም ሎካል / local mode / ካለ

መፍትሄው፡- ሀሏ ሞባይሉን ፍለሽ ማድረግ

ለሏ የሃርድዌር ችግር ከሆነ የባትሪ ኮኔክተር መሃል ላይ አሊያም አንዳንድ ጊዜ ዳር ላይ ሰለሚመጣ ቴምፕሬቸር የሚቆጣጠረውን ኮኔክተር ከነጋቲቩ ጋር በማገናኘት ቻርጀርን በመልቲ መጠቀም። አንዳንዴ ሶፍት ዌር ከተሰራላቸው በኃላ ስለሚለን ዲያግራም እያየን ማስተካከል እንችላለን።

+	ቴምፕሬቸር	-

- ኮንታንት service

መፍትሄ - ሶፍት ዌር

የሃርድዌር ችግር ከሆነ ሞባይሉን አጥቦ ፓወር አይሲንና ሲፒዩን በጥንቃቄ ማጠብ

ከቁጥር ጋር የተያያዙ ችግሮችን ማስተካከል

የስልካችን ቁጥሮች አልሰራም ሲሉ በተለያየ መልኩ መፍትሄ መስጠት ይቻላል።እንርሱም

ቁጥሮች አልፈው አልፈው የማይፅፉ ከሆነ

1. የቅጥሩን ላስቲክ መሰል አንስቶ ማስቲሹ እንዳይለቅ ከንፁህ ጠረንፔዛ ላይ መልተፍ ።ከዚያም የሞባይሎችን ቅጥሮች በዱለንቲን አፅድቶማሞቅ፡
2. የቁጥሮች በተን የሚያርፉበትን አልሙኒየም ማፅዳት አሊያም መቀየር።
3. .የቁጥር መረገጫውን ጎማ ቼክ ማድረግ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ስለምንጫነው ጎማው ሊበላ ስለመ ችል እሱን ማየት።

ቁጥሮች ወደ ጎን አሊያም ወደ ታች ሙሉ በሙሉ የማይፅፈ ከሆነ

ለምሳሌ 123 ወይም 2580

1. በማጠብ ለማስተካከል መሞከር
2. የቁጥር አይሲን ማሞቅ የቁጥር አይሲው መለያው ሲልቨር / ብርማሏከለርሏቀለምሏያለው ሆኖ የሚያንጸባርቅ ሲሆን አይሲው ሲነቀል 1. ባለ **24** እግር ሆኖ ከዳር አንድ እግር ሚጎድለው ሁኖ እናገኘዋለን።አይሲዋ **የምትገኘውየቁጥሮቹ መሰኪያ** አጠገብ

የቁጥሮች ማረፊያ አካባቢ

ሲፒዩ አጠገብ ይገኛል

ነጻ ቦታ ላይ ሆኖ ከሲምኮኔክተር አጠገብ

የቁጥሮቹ መሰኪያ አጠገብ

3. ከአንዳንድ የቻይና ሞባይሎች ላይ የቁጥር ኬብሉን ቼክ ማድረግ

<u>ቁጥሮች ወደ ጎን ወይም ወደታች የተወሰኑት ቁጥሮች አልሰራም ከአሉ</u>

እንደሞባይሉ የተለያየ ቢሆንም

1. ወደታች ውስጥ ለውስጥ ስንለካ ቁጥር ከአነበበ ወጭ ለውጭ ደግሞ ድምፅ መስጠት አለበት
2. እንዲሁም ወደጎን ውስጥ ለውስጥ ድምፅ ከሰጠን ውጭ ለውጭ ቁጥር መስጠት አለበት።በመሆኑም ከላይ በተገለፀው መሰረት ካላገኝን በጃምፐር ጃምፕ ማድረግ።


<u>6.የሞባይል ስዊች ሲበላሽ</u>

የሞባይል ሰዊች ከተበላሸ ሞባይሉ ሊነሳልን አይችልም በመሆኑም

<u>ስዊቹን መካኒካሊ መለካት ።አለካኩም</u>


የሞባይል ማብሪያ ማጥፊያ


- የሞባይል ማብሪያ ማጥፊያ ስንል በዚህ ውስጥ የምንረዳው በጎን በኩል አሊያም በላይ በኩል ማብሪያ ማጥፊያ ያለውን ነው።
- ማብሪያ ማጥፊያ መስራት አለመስራቱን ለማረጋገጥ በጀመሪያ ሜትሩን ኮንቲኒቲ ላያ ማድረግና ላይናታች አለበለዚያ ከላይኛው ማዕዘን ወደታችኛው ማዕዘን እየለካን ማብሪያ ማጥፊያ ስንጫን የሚጮህ ከሆነ ማብሪያ ማጥፊያው መስራቱን እናረጋግጣለን የማይጮህ ከሆነ አለመስራቱን እናረጋግጣለን ።




ከላይ እንደተገለጸው መለካት ያለብን AC ወይም BD ወይም AD ወይም BD ላይ የዘን ማብሪያ ማጥፊያው ስንጫን ነው መስራት አለመስራቱን የምናረጋግጠው ከዚህም በተጨማሪ የሚሠራ ማብሪያ ማጥፊያ ከሆነ ከማብሪያ ማጥፊያው ላይ ስንለካ 3.6V እናገኛለን። ከአገኘን በኃላ ማብሪያ ማጥፊያውን ስንቻነው ከ 3.6V ወደ 0V ይቀንሣል። በላይ በኩል ወይም በጎን በኩል ያለው ማብሪያ ማጥፊያ ከተለያዩ ኤሌክተሮኒክስ ካምፓነንት ጋር ተያይዘው እናገኛለን። በተለይ ብዙ የማብሪያ መስመሮች ከሬዚስተር ከካፓሲተር ከኮንዳክተር ጋር የተያያዙ ናቸው። በመሆኑም መስመሮችን በሙሉቸክ መደረግ አለባቸው ለምሳሌ:-

6.1 ስዊች ባለ አራት እግር ከሆነ








ሜትራችን ከ1 እና 3 ወይም 1 እና 4 ወይም 2 እና 4 ወይም 2 እና 3 ላይ ብናያይዘው ሞባይሉ አውቶማቲካሊይነሳል፡፤ነገር ግን እንደሞባይሉ ሁኔታ የማይነሳና ተነስቶ የማይሰራ ሊያጋጥም ስለሚችል ስዊቹን ማስቀመጥ የግድ ይለናል።

6.2 ስዊች ባለ ሁለት እግር ከሆነ




ሜትራችን 1 እና 2 ላይ ይዘን ስዊቹን ስንጫነው ድምፅ መስጠቱን እናረጋግጣለን

ስለዚህ ባለ አራትሏ4/ እግር ወይም ባለ ሁለት / 2/ እግሮች ኮንቲኒቲ የማይሰጡ ከሆነ ወይም በአይን ስናይ የተሰበረ ከሆነ ስዊቹን መቀየር።

1. **<u>የስዊችን መንገድ መከተል</u>**

የስዊች መንገድ እንደየሞባይሉ ቢለያይም ረዥሙ የስዊች መንገድ



ስለዚህ በኮንቲኒቲ ልንለካ የምንችለው።

1. ከስዊች እግር እሰከ ኢንዳክተር ድረስ መለካት
2. ኢንዳክተርን መለካት
3. ከኢንዳክተር እስከ ካፓሲተር መለካት እንዲሁም ከእንዲአክተር እስከ ረዚስተራ ድረስ መለካት
4. ካፓሲተርን መለካት
5. ረዚስተርን መለካት

- በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት የሚሰሩ ከሆነ እና ፓወር አይሲ የሚሰራ ከሆነ ለሞባይሉ ፓወር ተሰጦት ከስዊቹ እግረ ላይ 3.6 ቮልቴጅ መምጣት አለበት።ነገር ግን መንገዶች ንፁህ ሁነው ከስዊች ላይ 3.6ቮቴጅ የማይደርስ ከሆነ ፓወር አይሲን በጥንቃቄ ማሞቅ።እንደዚህም ሁኖ ካልመጣ ለዚህ ችግር ተጠያቂ ከሚሆኑት መካከል ለምሳሌ፡-

1. ራሱ ፓወር አይሲ
2. ሲፒዩ / cpu/ አይሲን
3. ሚሞሪ / memory/ አይሲን ከማሞቃችን በፊት መጀመሪያ ስልኩን ፍለሽ ማድረግ

1. ፍለሽ ስናደርግ ፍላሽ ጨርሶ የሚቀበል ከሆነ መጀመሪያ ሲፒዩን / cpu/ ን ማሞቅ

2. ፍለሽ ጀምሮ የሚያቃርጥ ከሆነ ግን መጀመሪያ ራሱን ፍለሽ አይሲን ማሞቅ።
3. መጨረሻ ላይ ግን ችግሩ ያለው አሁንም ራሱ ፓወር አይሲ ላይ ነው። ስለዚህ ራሱን ፓወር አይሲን መቀየር።

6.3 ከፓወር ጋር ከተያዙ ችግሮች መካከል።

ሾርት ሰርኪዊት ወይም መገናኘት የሌለበት መስመር ወይም እግር ተገናኝታል ማለት ነው።

ሾርት ሰርኪዊትን እንዴት ማስተካከል ይቻላል

1. መጀመሪያ ሾርት ሲያደርግ የሚችለዉ ውሃ ውስጥ ገብቶ ሊሆን ስለሚችል በዱለንቲን ማጠብ ወይም ማጽዳት።
2. በዲሲ ፓወር ሰፕላይ ፓወር ሰጥቶ የሚግሉትን አይሲዋች መፈለግ። ስንፈልግ ያገኘነው ወይም የሚግለው አይሲ መቀየር የሚችል ከሆነ መቀየር ሲሆን የሚግለው ግን መቀየር የማይችል ከሆነ ስልኩን መመለስ ነው።
3. የሶፍት ዌር ችግር ሲሆን
   - የሶፍት ዌር ችግር ላለበት ስልክ መፍትሄው ፍለሽ ማድረግ ነው። ሌላዉ ደግሞ

የሚሠራ ስልክ ሲሆን ችግሩ ሊሆን የሚችለው ግን፡-

1. ለማንኛውም ሥልክ ግን ማለትም ለታጣፊም ስላይድም (ለሻተር) ወይም ለኖርማል ስልኮች መጀመሪያ ስክሪኑን ቼክ ማድረግ ነው ምክንያቱም አንዳንድ ስልኮ ለመብራት ስክሪን ስለሚፈለጉ።

7.የቻርጀር ችግር

1. ቻርጀርን ቸክ ማድረግ
2. ባትሪን ቸክ ማድረግ ማለትም ቻርጅ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ቮልቴጅ መኖርና አለመኖሩን በሜትር ለክቶ ማረጋገጥ።ቮልቴጁ በጣም አነስተኛ ከሆነ ሲ ዲሲ አዳፕተር ማስነሳት።
3. ቻርጅር ኮኔክተሩን በአይን አይቶ የተጣመመ ከሆ ማቃናት ፣ተቆረጠ ከሆነ መቀየር እንዲሁም ዝገት ካለ ማፅዳት።
4. የቻረጀር ኮኔክተሩ ዝገት ካለበት ማፅዳት።
5. የቻረጅረ ኮኔክተሩ መቀመጫ ዝገት ካለበት ወይም በትክክል አለመገናኘት ካለ ማስተካከል።
6. የቻረጀ ፡፤ርን መንገድ በፈተሸ።

ቼክ ስናደርግ ፊዱዝ ድምጽ መስጠት አለባት

+ ፊዩዝ ኢንዳክተር

K L

የቻርጀር መስመሩን ለመፈተሽ ፊውዝን ፣ኢንዳክተርን፣ዳዮድን እና ካፓሲተርን መፈተሽ።አፈታተሽም

ከቻርጅ ማረፊያ ፓዘቲቩ እስከ ፊውዝ ራሳ ከፊውዝ እስከ ኢንዳክተር ራሳ ከኢንዳክተር እሰከ ዳዮድ ፓዘቲቭ እግር ከኢንዳክተር እሰከ ካፓሲተር ፖዚቲቭ እግር ድረስ ኮንቲኒቲ ወይም ድምጽ መስጠት አለበት። ድምጽ የማይሰጥ ከሆነ ግን የተቃረጠ መስመር ጋር ጃምፐር ዋየር መጠቀም ዳዮድ ደግሞ በሁለቱም በኩል አንድ ወይም ድምጽ የሚሰጥ ከሆነ መቀየር ነው። ከዚህ ግን ካለፈ ችግሩ ያለው እዛው ቻርጅ አይሲ ላይ ነው።ነገር ግን በዲሲቲ 4/ አራትሏእና 3/ ሶስትሏስልኮች ጊዜ አይሲውን መቀየር። ነገር ግን በቢቢ5/ አምስትሏስልኮች ጊዜ ግን ችግሩ ያለው ፓወር አይሲላይ ስለሆነ መፍትሄው መልቲ ቻርጀር መጠቀም ነው።

ከቻርጀር ጋር ከተያያዙ ችግሮች መካከል ቶሎ ቶሎ ባትሪ የሚጭርስ ስልክ ከሆነ

1. መጀመሪያ ባትሪውን ቼክ ማድረግ
    - ያበጠ ከሆነ ባትሪ አበጠ ማለት ሾርት አለ ማለት ሲሆን ይህ ማለት ደግሞ ፓዘቲቭና ኔጊቲቭ የተገናኙ ከሆነ የባትሪው ቮልቴጅ ወደ ግራውንድ እየፈሰሰ ያልቃል ማለት ነው።
    - ቀጥታ ከባትሪ ቮልቴጅ ወይም ፓወር የሚያገኙትን አይሲዎች ቼክ ማድረግ ከነዚህም መሀል ፓወር አምፒሊፋየርና ፊልተር ካሲተሩን እንደዚሁም ፓወር አይሲውን አጅበውት ከሚገኙት ፊልተር ካፓሲተሮች መካከል ሾርት ያደረገ ካለ ቼክ ማድረግ
    - ቼክ ስናደርግ ካፓሲተሮች ኮንቲኒቲሏድምጽሏበፍጹም መስጠት የለባቸውም ምክንያቱም ካፓሲተሮች አንዱ እግራቸው ግራውንድ ጋር የታሰረ ስለሆነ ሾርት ካደረገ ድምጽ ስለሚሰጥ የሚሰጠውን ካፓሲተር ነቅሎ መቀየር
    - ካፓሲተሮችን ቼክ ስናደርግ ኮንቲኒቲ የማይሰጡ ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ ሾርት የሚያደርገው ፓወር አምፒሊፋየር ስለሆነ እሱን ተቅሎ መሞከር ፓወር አምፒሊፋየሩን ከለቀቀ ፓወር አምፕሊፋየርን መቀየር ነው።

ፓወር አምፕሊፋየርን ስንነቅለውና ከለቀቀ ችግር የሚኖረው ከፓወር አይሲው ስለሆነ መፍትሄው የሚሆነው ሁለት ኦርጅናል ባትሪ መጠቀም ነው።

ቻርጅ ሲደረግ የሚግልሏየሚሞቅሏስልክ ሲሆን

መፍትሄውም

1. መጀመሪያ አሁንም ባትሪውን ቼክ ማድረግ ያበጠ ከሆነ

2. የቻርጀር መሰኪያ ላይ ያሉትን ሁለቱን እግሮች ማለትም ፓዘቲቩንና ነጌቲቩን እግር መገናኘታቸውን በድምጽ ቼክ ማድረግ በፍጹም መገናኘት የለባቸውም።

3. በቻርጀር ከረንት በሚያልፍበት መስመር ላይ ያለውን ዳይዱን ቼክ ማድረግ ምክንያቱም ዳዮድ በፍጹም ኮንቲኒቲ / ድምጽሏ መስጠት ስለሌለበት

4. መጨረሻ ላይ ችግሩ የሚሆነው ፓወር አይሲ ጋር ስለሆነ መፍት መልቲ ቻርጀር መጠቀም ነው::

5. ባትሪዉ ተሎ ተሎ የሚያልቅ ከሆነ የቫይረሥ ጭግር ሊሖኝ ሥለሚጭል ባጥሪውኝ በለላ ሞባይል ሞክሮ ባትሪው ሌላ ሞባይል ላይ ጦሎ ጦሎ የማያልቅ ከሆነ ሞባይሉን ፎረማት ማድረግ።ለምሳሌ ኖኪያ **N71/ 73** የመሣሠሉጥ ሞባይሎች ***#7370#*** የቫይረስ ማጥፊያ ነው።

ስልኩን ቻርጅ ስናደርግ ስክሪኑ ላይ

1. ቻርጅ ማድረጉን አቁም

2. ቻርጅ አላደርግም ካለ ሲስተም ውስጥ

Setting - enheancement- ውስጥ ያሉትን እቀያየሩ መሞከር ። ምክንያቱም አንዳንድ ሞባሎች ቻርጀር የሚለው ከተመረጠ በሌላ ባትሪ ቻርጅ ላያደርጉ ይችላሉ።

3. ቻርጀሩን አልቀበለውም ሲል

የሚል ከሆነ መጀመሪያ ቻርጀሩን ራሱን ቼክ ማድግ ምክንያቱም አንዳንዱም ስልኩ የራሳቸው ቻርጀር ካልሆነ በስተቀር በሌላ ቻርጀር ስለሚያስቸግሩ።

- ቀጥሎ ደግሞ ባትሪውን ቼክ ማድረግ ምክንያቱም አሁንም አንዳንድ ስልኮች ከራሳቸው ሞዴል ባትሪ በስተቀር በሌላ ባትሪ ቻርጅ ማድረግ ሰለማይችሉ ባትሪ እየቀየሩ መሞከር

- መጨረሻ ላይ ግን ችግሩ ሊኖር የሚችለው ቻርጅ አይሲው ጋር ነው።

  መፍትሄው ለዲሲቲ 3 ኖኪያ፣ለሳምሰንግ፣እና ለቻይና ሞዴል ስልኮች ቻርጅ አይሲን መቀየር። ነገር ግን ሰዲሲቲ 4 ና ለቢቢ5 ስልኮች ችግሩ ያለው ፓወር አይሲጋር ስለሆነ መፍትሔው

  መልቲ ቻርጀር መጠቀም

  1- ብዙዎች የኖኪያ ቻርጅ አላደርግ ሲል “Not charging” ይላል። በዚህን ጊዜ የሀርድ ዌር ችግር ነው።

  2- Reconnect charge ▶ ሄም የሃርድ ዌር ችግር ነው ማለትም የኮምፓነንት መበላሸት ነው

  3- ከሞባይ እስክሪን ላይ ቻርጅ እያደረገ ነገር ግን ባትሪው አልሞላ ከአለ

     a. የአረጀ ባትሪ ሊሆን ስለሚችል ቀይሮ ማየት

     b. በኮምፒዩተር ማስተካከል

  4- ከሞባይል እስክሪን ላይ ቻርጅ መሙላቱን አይተን ጥሪ በምንቀበልበት አሊያም በምንደውልበት ጊዜ ሞባይሉ የሚጠፋ ከሆነ

a. ፓወር አምፕሊፋየር እናሞቃለን

b. የባትሪ ኮኔክተር ከቦርዱ ጋር ተገናኝቶ ከሆነ እናስተካክላለን

c. የጠፋውን ሞባይል ስናስነሳው ባሪው ባዶ ከሆነ የባትሪ ችግር ስለሆነ ባትሪውን መቀየር።

d. ከላይ በተጠቀሱት አልሠራም የሚል ከሆነ በኮምፒውተር እናስተካክላለን።

ማጠቃለያ:- ሞባይል ቻርጅ አላደርግ ካለ መጀመሪያ ቻርጀር መስራቱን ማረጋገጥ እንዲሁም ባትሪው ቻርጅ የማድረግ አቅም መኖሩን አለመኖሩን በትክክል መረዳት ባትሪው የመነሣት አቅም ከሌለው በአዳፕተር እናስነሳዋለን።

በአጠቃላይ ለሞባይሉ ቮልቴጅ ሰጥቶ ከባትሪኮኔክተሩ ላይ

<u>3.6 ቮልቴጅ መጥቶ ቻርጅ አላደርግም ካለ</u>

መፍትሄው፤

- ማፅዳት
- ባትሪ ቀይሮ ማየት
- ዲያግራም ተከትሎ 47KΩ የምትመጣውን ትራንዚስተር ቼክ ማድረግ

<u>ከ3.6ቮልቴጅ በታች መጥቶ ቻርጅ አላደርግም ካለ</u>

- ቻርጀር አይሲን ማሞቅ

አንድሮይድ ሚስጥራዊ ኮዶች!
*#06# – የ IMEI ቁጥር ለማሳየት ይጠቅማል
*2767*3855# – ሞባይሉ ፎርማት ለማድረግ(ይህ ኮድ በሞባይሉ ላይ ያለ ማንኛውም ነገር ያጠፈዋል ስለዚህ የሞባይል ቴክኒሻን ብቻ ቢጠቀምበት).
##7780#*#* - ይህ ሞባይል ወደ ቀድሞ የነበረበት ይዞታ ይቀይረዋል የጎግልና ሌሎች አፕሊኬሽኖች ይጠፋሉ
ፋይሎትን backup ለማድረግ: *#*#273282*255*663282*#*#*
ስለ ካሜራ መረጃ: *#*#34971539#*#*
ስለ ስልኮ Software & Hardware መረጃ: *#12580*369#
ዝርዝር መረጃው እንሆ ያንብቡት

http://www.zinktube.net/article_read.php?a=129

List of secret codes for Android

These codes are mostly universal and should work on Android devices, no matter the manufacturer. There might still be carrier restrictions on certain codes though, so they're not all guaranteed to work.

Info codes

CODE	FUNCTION
*#06#	Showphone's IMEI
#0#	Info menu (doesn't work for all phones)
##4636#*#*	Info menu
##34971539#*#*	Camera info
##1111#*#*	FTA software version
##1234#*#*	PDA software version
*#12580*369#	Software and hardware info
*#7465625#	Device lock status
##232338#*#*	MAC address
##2663#*#*	Touchscreen version
##3264#*#*	RAM version
##232337#*#	Bluetooth address
##2222#*#*	Hardware version
##44336#*#*	Software version and update info

Backup codes

CODE	FUNCTION
##273282*255*663282*#*#*	Backup all media

Testing codes

##197328640#*#*	Test mode
##232339#*#*	Wi- Fi test
##0842#*#*	Brightness and vibration test
##2664#*#*	Touchscreen test
##232331#*#*	Bluetooth test
##7262626#*#*	Field test
##1472365#*#*	GPS quick test
##1575#*#*	Full GPS test
##0283#*#*	Packet loopback test
##0*#*#*	LCD display test
##0289#*#*	Audio test
##0588#*#*	Proximity sensor test

Configuration codes

CODE	FUNCTION
*#9090#	Diagnostics settings
*#301279#	HSDPA/ HSUPA settings
*#872564#	USB logging settings

Developer codes

CODE	FUNCTION
*#9900#	System dump mode
##778 (+green/ call button)	EPST menu

Manufacturer- specific codes

Motorola

CODE	FUNCTION
##7764726	Hidden Motorola Droid menu

HTC

CODE	FUNCTION

##3424#*#*	HTC test program
##786#	**(Caution!)** Phone reset menu
##3282#	EPST menu
##3424#	Diagnostic mode
##33284#	Field test
##8626337#	Launch Vocoder
##4636#*#*	HTC info menu

Other codes


CODE	FUNCTION
*#7780#	**(Caution!)** Factory reset
*2767*3855#	**(Caution!)** Full factory reset
##7594#*#*	Power off the phone
##8351#*#*	Activate dialer log mode
#*#8350#*#*	Disactivate dialer log mode

Stay away from these codes (Caution! Risk of data loss and rendering phone useless)

CODE	FUNCTION
~~*#*#7780#*#*~~	**(Caution!)** Factory data partition reset
~~*2767*3855#~~	**(Caution!)** Format device

There's a good chance you'll never need to use these codes, but if you do then nowyou knowwhere to find them.

Are there any secret codes that you find yourself using all the time? Or are there any we haven't listed here that are really interesting? Let us knowin the comments!



Related Articles

- *Easy ways to dramatically reduce your mobile data usage on Android*

  1. Restrict background dataThe easiest way to save data is to tell your apps (or the Android system itself) to restrict ba…

- *10 Simple Ways To Reduce Data Usage On Your Android Device*

  10 Simple Ways To Reduce Data Usage On Your Android Device Nowadays network carriers are so intelligent that they have re…

- *Minimize Mobile internet Fee's*

  Smart phones and mobile internet have changed our lives. They have become an integral part of our lives and we heavily dep…